**የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም**
**መመሪያ ቁጥር 234/2013ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ**

የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 (ን) ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፣

መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 234/2013ን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ መደብ (ሀ) አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. አንቀጽ 2(ረ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 2(ረ) ተተክቷል፡፡
   ረ/ "የምስክር ወረቀት ሰጪ አካል" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስቴሩ የሚወክለው ሌላ ማንኛውም አካል ነው፡፡

2. አንቀጽ 2 (ወ) ተሠርዟል፡፡

3. አንቀጽ 2(ዘ) እና (ዠ) እንደቅደም ተከተላቸው አንቀጽ 2(ወ) እና (ዘ) ሆነዋል፡፡

4. አንቀጽ 6 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6 ተተክቷል፡፡

   **6. የምስክር ወረቀት የሚሰጥ መስፈርት**

   የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል አምራቹ የሚከናወናቸው ሥራዎች በአንቀጽ አምስት መስረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችሉ ያለመሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ የተጨማሪ እሴት መጠኑን በአባሪ ሠንጠረዡ ላይ በተዘረዘረው መስረት በማገናም የኢንዱስትሪ ንዑስ ዘርፉን የተጨማሪ እሴት መጠኔ መስፈርት ሙሉ ለሙሉ ለሚያሟሉ አምራች የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ሀ) ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

5. አንቀጽ 7 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 7 ተተክቷል፡፡

   **7. የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ**

   የምስክር ወረቀት ሰጪው አካል አመልካቹ የተሰማራበት ሥራ ከላይ በአንቀጽ አምስት ከተዘረዘሩት ወስጥ ያለመሆኑን በሚያጋገጥ እና አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ብቻ

ጥያቄወን በታሪፍ አንቀጽ ለውጥ ማስፈርት መሠረት ይገመገማል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ ሟቢብ (ሀ) የታሪፍ ማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን፡ –

ሀ/ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ ለማምጣት የምርት ሂደት ተከናወኖባቸው በሜጨረሻ የሚገኘወን ምርት የሚያስገኙ ወደሀገር ወስጥ የሚገቡ ግብዓቶች የሚመደቡበት የታሪፍ አንቀጽ በሜጨረሻ የሚገኘው የምርት ወጤት ከሚመደብበት የታሪፍ አንቀጽ በተለየ የታሪፍ አንቀጽ ላይ የሚመደቡ መሆን አለባቸው፡፡

ለ/ የምርት ሂደት ተከናወኖባቸው በሜጨረሻ የሚገኘወን ምርት ከሚያስገኙ ግብዓቶች ወስጥ አንዳቸው እንኳን በሜጨረሻ የሚገኘው የምርት ወጤት የሚመደብበት የታሪፍ አንቀጽ ላይ የሚመደቡ ከሆነ የታሪፍ አንቀጽ ለውጥ እንደተደረገ ስለሚይቆጠር የታሪፍ ማበረታቻው ተጠቃሚ መሆን አያስችልም፡፡

ሐ/ ፈቃድ ሰጨው አካል በታሪፍ አንቀጽ ለውጥ ማስፈርት መሠረት የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ ሟቢብ ጥያቄዎችን ለመገምገም የምርቶችንና የግብዓቶችን የታሪፍ አመዳደብ በተመለከተ የባለሥልጣኑን መ/ቤት የሙያ እገዛ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

መ/ የባለሥልጣን መ/ቤቱ በፈቃድ ሰጨው አካል የምርቶቹን እና የግብዓቶቹን የታሪፍ አመዳደብ በተመለከተ የሙያ እገዛ ሲጠየቅ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

6. አንቀጽ 25(ለ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 25(ለ) ተተክቷል፡፡

ለ/ ማንኛውም ነባር የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ ሟቢብ(ሀ) ተጠቃሚ አምራች ድርጅት መመሪያው እስከሚፀናበት መስከረም 2/2009 ዓ.ም ድረስ በመመሪያው መሠረት አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት የተጠቃሚነት የምስክር ወረቀት በማግኘት ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ማቅረብ አለበት፡፡

## 3. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

የጉምሩክ ታሪፍ ደንብ ሁለተኛ ሟቢብ (ሀ) አጠቀቀም መመሪያ ቁጥር 45/2008 ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ መስከረም 2 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ እንዲሆን ተራዝሟል፡፡

አዲስ አበባ ሰኔ 23 ቀን 2008 ዓ.ም.

አብዱልአዚዝ ማሐመድ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር